# የኢትዮጵያን ልጆች ለመጠበቅ የሚደረግ የፊርማ ማሰባሰብ!

እኛ ከታች የፈረምን ወላጆች ፣ አያቶች ፣ አስተማሪዎች ፣ ሐኪሞች ፣ በሌሎች ልዩ ልዩ ሞያዎች የተሰማራን ፕሮፌሽናሎች ፣ አማካሪዎች ፣ ነጋዴዎች ፣ የሃይማኖት እና የህብረተሰብ መሪዎች ከ"የኢትዮጵያን ልጆች እንታደግ ጥምረት" ወይንም "Protect Children Ethiopia Coalition" ጋር በመተባበር ሁሉን አቀፍ የወሲብ ትምህርት Comprehensive Sexuality Education (CSE)) በመባል የሚታወቀውን የትምህርት ዓይነት በኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ተካትቶ በመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተግባራዊ ሊደረግ መታቀዱን በሚቀጥሉት ሰባት ምክንያቶች አጠንክረን እንቃወማለን ፡፡

1. ሁሉን አቀፍ የወሲብ ትምህርት (CSE) ከኢትዮጵያ ባህላዊ እሴቶች ጋር ፈጽሞ የሚጣረስ ነው። ኤች አይ ቪን እና በአሥራዎቹ ዕድሜ የሚገኙ ታዳጊ ሴቶችን ርግዝና መከላከልን በማመካኘት የኢትዮጵያን የጾታ እና የወሲብ ሥነ-ምግባርን ለመለወጥ የሚፈልግ አደገኛ የሆነ በምዕራባዊያን መንግስታትና በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሚመራ አጀንዳ ነው ፡፡ በርካታ የተባበሩት መንግስታት ድርጅቶች በ"International Technical Guidance on Sexuality" በሚለው እኤአ የ2018 ህትመታቸው ላይ "በመብቶች ላይ የተመሠረተ" ብለው የሚያቀነቅኑትንና ጎጂ የሆነውን አጥፊ የወሲብ አጀንዳቸውን በግልፅ አሳይተዋል ፡፡ ይኸውም በሁሉን አቀፍ የወሲብ ትምህርት (CSE) ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች በጨራሽ የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዳይፈጽሙ ከማስተማር ይልቅ አንድ ልጅ "መቼ እና ከማን ጋር" ወሲብ ማድረግ እንዳለበት መወሰን ይችላል የሚለውን ፅንሰሀሳብ እንደሚያራምድ በህትመቱ ላይ አሳይተዋል ፡፡ በተጨማሪም ጎጂ የሆነ የጾታዊ ማንነት ርዕዮተ ዓለምን ፣ ወሲባዊ ሴሰኝነትን እና ውርጃን ያበረታታል ፡፡ ልጆች ከወላጆቻቸው የተለዩ ወሲባዊ እሴቶች እንዲኖራቸው እና በጾታዊ ግንኙነት ረገድ ማህበራዊ ተቀባይነት ያላቸውን ደንቦችና እሴቶች ጥያቄ ውስጥ እንዲያስገቡ ይጠይቃል ፡፡
2. ያለወላጅ ተሳትፎ ፣ መመሪያ እና ፈቃድ ሁሉን አቀፍ የወሲብ ትምህርት (CSE) ካሪኩለምን ማውጣት በዓለም አቀፍ ህግ የተቀመጡ የወላጆች መብቶችን ይጥሳል። ኢትዮጵያ ፈራሚ የሆነችባቸው በርካታ ወሳኝ እና ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሰነዶች እንደሚደነግጉት ወላጆች የልጆቻቸውን የትምህርት ይዘት የመወሰንና የመምራት "ቀዳሚ መብት" አላቸው ፡፡ ይሁንና የኢትዮጵያ ወላጆች በሥርዓተ ትምህርታችን ውሥጥ እንዲካተት ግፊት እየተደረገበት ያለውን ወሲብ ነክ ሥርዓተ ትምህርትን የማየትና የመገምገም ዕድል አልተሰጣቸውም።
3. UNFPA የተባለው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ኤጀንሲ ፣ ከሌሎች የተባበሩት መንግስታት ኤጄንሲዎች እና የውጭ መንግስታት ጋራ በመተባበር በኢትዮጵያ እና በተቀሩት የአፍሪካ ሐገራት ውስጥ ሁሉን አቀፍ የወሲብ ትምህርት (CSE)ን የመተግበር አጀንዳ እየመሩ ይገኛሉ ፡፡ ለምሳሌ UNFPA በስዊድን

መንግሥት የገንዘብ ድጋፍ በተዘጋጀውና እና “Basic and Higher Institutions of Learning in KwaZulu-Natal” በተሰኘውና ደቡብ አፍሪካን አስመልክቶ ባዘጋጁት ህትመታቸው (ለመመልከት https://southafrica.unfpa.org/sites/default/files/pub-pdf/UNFPA_CSE_report_web.pdf)

በሀገር አቀፍ ደረጃ ሁሉን አቀፍ የወሲብ ትምህርት (CSE) ተፈጻሚ እንዲሆንይጠይቃል። በተጨማሪም እጅግ አወዛጋቢ ለሆኑት ጉዳዮች ማለትም ለወሲባዊ ዝንባሌ (sexual orientation) ፣ ለጾታዊ ማንነት (gender identity) ፣ የወሲባዊ ስሜት አገላለጥ ልዩነት (sexual diversity) እና ለሁሉም የወሲብ ምርጫዎች (sexual preference) አክብሮት የመስጠትን ጉዳይ ትኩረት እንዲሠጠው ይጠይቃል ። ከዚህ በተጨማሪም በኩል ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች በጭራሽ የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዳይፈጽሙ ከማስተማር ይልቅ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ግብዣን አልፈልግም ብሎ የመመለስ መብት እንዳላቸው በዚሁ በሁሉን አቀፍ ጾታዊ ትምህርት (CSE) አማካኝነት ያስተምራል።

በወሲባዊ ተግባር የሚሳተፉ በአስራዎቹ የዕድሜ ክልል ያሉ ልጆች ብዙውን ጊዜ የሚከተሉት አሉታዊ ውጤቶች ያጋጥሟቸዋል።

- የርግዝና መከላከያ የመጠቀም ዕድላቸው አነስተኛ ነው፤
- በተላላፊ የአባለዘር በሽታዎች የመያዝ ዕድላቸው ሰፊ ነው፤
- የአሁን ወይንም የህይወት ዘመን የወሲብ ጓደኛዎቻቸው በርካታ ይሆናሉ፤
- የማርገዝ ዕድላቸው ሰፊ ነው፤
- ትምህርት ማቋረጥ (ከእርግዝና ጋር ባይገናኝ እንኳን)፤
- የወሲባዊ ጥቃት ሰለባነት መጨመር፤
- ድብርትን (Depression) ጨምሮ አጠቃላይ የአካላዊ እና የሥነ-ልቦናዊ ጤና መቃወስ፤
- መልካም እና የተረጋጋ ግንኙነት የመመሥረት እድላቸው ዝቅተኛ ሲሆን የመፋታት እድላቸው ደግሞ ከፍተኛ ነው፤
- እንደ ማጨስ ፣ መጠጥና አደንዛዥ ዕጾች ባሉ ሌሎች የአደጋ ተጋላጭነቶች ላይ ከፍ ያለ ተሳትፎ፣
- ከማህበራዊ ህይወት መራቅ ወይም በግለኝነት ባህሪ የመሰተፍ እድላቸው ሰፊ ነው፤
- በራሳቸው ውጤታማ የመሆን እና ራስን የመቆጣጠር ዕድላቸው አነስተኛ ነው፤
- ከወላጆች ፣ ከት/ቤት እና ከእምነት ጋር ቁርኝታቸው ይቀንሳል፤

4. በተባበሩት መንግስታት ኤጀንሲዎች እና በምዕራባዊ መንግስታት የሚደገፉትን ጨምሮ የሁሉን አቀፍ የወሲብ ትምህርት (CSE) መርሃግብሮች ከወሲባዊ ጤና (sexual health) ይልቅ “ወሲባዊ መብቶች” (sexual rights) ላይ ትኩረት በማድረግ ሞራላዊ የሆነ የወሲባዊ ትምህርት አቀራረብን ሳይሆን ፣ አወዛጋቢውንና በ“መብቶች ላይ የተመሠረተ” አካሄድን ይከተላሉ።

5. ኢትዮጵያ አወዛጋቢውን “Ministerial Commitment on Comprehensive Sexuality Education and Sexual and Reproductive Health and Rights for Adolescents and Young People on Eastern and Southern Africa (ESA)” የሚባለውን ሰነድ ስትፈርም ከሚመለከታቸው የመንግስት አስፈጻሚ አካላትና ከሁሉም በላይ ደግሞ ልጆችን የማሳደግ ቀዳሚ ኀላፊነትና አደራ ካለባቸው ከወላጆች ጋራ አስፈላጊ የሆነ ምክክር አለማድረ□ ወላጆች የልጆቻቸውን ትምህርት እንዲመሩ የተሰጣቸውን መብት ወደጎን ያደረገ ነው።

6. “National Adolescent Sexual and Reproductive Health and Rights (ASRHR) Framework Strategy” የተባለውም ሰነድ እንዲሁ ለምምክር ያልተጠሩ ወላጆችን መብቶቻቸውን የጣሰ ሲሆን የተባበሩት መንግስታትንና እና የምዕራባዊያንን ከወሲባዊ ጤና (sexual health) ይልቅ “ወሲባዊ መብቶች” (sexual rights) ላይ ያዘነበለውን አቋማቸውን የሚያንፀባርቅ ነው። በዓለም ዙሪያም በተባበሩት መንግስታት ወኪሎች የወላጆችን መብት የጣሱ ተመሳሳይ ስትራቴጂዎች ወደፊት እየተገፉ ናቸው ።

7. ከሁሉም በላይ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ኤጀንሲዎች ሁሉን አቀፍ የወሲብ ትምህርት (CSE) ውጤታማ እንደሆነ እና በአሥራዎቹ ዕድሜ ክልል የሚገኙ ልጆችን እርግዝና እና HIVን ጨምሮ በግብረሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን እንደሚከላከል እንዲሁም መታቀብ ደግሞ በተቃራኒው ውጤታማ እንዳልሆነ ያስረዳል ሲሉለት የነበረው “ጥናት” በቅርቡ በአንድ ሌላ ዓለም አቀፍ በሆነ ጥናት ፈጽሞ ከእውነት የራቀና ተቀባይነት የሌለው እንደሆነ ተረጋግጧል። በSexEdReport.org ላይ ሪፖርት በተደረገው አዲስ ዓለም አቀፍ ትንታኔ መሠረት ሁሉን አቀፍ የወሲብ ትምህርት (CSE) በከፍተኛ ሁኔታ ማለትም በ87 ፐርሰንት ያህል የወደቀው ወይንም ውጤት አልባ የሆነው በአፍሪካ ውስጥ እንደሆነ እንዲሁም ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ (24%) ያስከተለውም አፍሪካ ውስጥ እንደሆነ ተረጋግጧል። ይህንን “Re-Examining the Evidence for Comprehensive Sex Education in Schools – A Global Research Review,” በሚል ርዕስ የወጣው ጥናት ውስጥ የተካፈሉት ተመራማሪዎች በUNESCO እንደ አስረጂ የተጠቀሰውን ምርምር ተመልክተው የሚከተለው ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል።

   “በሶስት አስርት ዓመታት ውስጥ በተደረጉ ምርምሮችና ጥናቶች መሠረት ት/ቤቶችን ያማከለ ሁሉን አቀፍ የወሲብ ትምህርት(CSE) ውጤታማ የህዝብ ጤና አጠባበቅ ስትራቴጂ መሆን እንደማይችል ተረጋግጧል፤ በአሜሪካ እና ከአሜሪካ ውጭ ከመከላከል ጋራ በተያያዘ በጣም ውሱን የሆኑ ዘላቂ ውጤቶችን ብቻ

አስገኝቷል ። በእርግጥም ሁሉን አቀፍ የወሲብ ትምህርት ማለትም CSE ከስኬት ይልቅ እጅግ የላቀ ውጤት አልባነትን(failure) አሳይቷል፤ በርካታ ጉዳቶችንም ማስከተሉም ተረጋግጧል…

አጥኝዎቹ በስተመጨረሻ የሚከተለውን ብርቱ ማሳሰቢያ እንደሚከተለው አስተላልፈዋል፣

"በግብረሥጋ ግንኙነት ተላላፊ የሆኑ በሽታዎችና እርግዝና በዓለም ዙሪያ ለወጣቶች ጤና እና ደህንነት ስጋት መሆናቸውን ስናይ ፤ ወደ 30 ከሚጠጉ ዓመታት በኋላና እና 103 ከሚሆኑ ተዓማኒነት ካላቸው ጥናቶች በኋላ የደረስንበት ድምዳሜ ትምህርት ቤቶችን ያማከለ ሁሉን አቀፍ የወሲብ ትምህርት ፈጽሞ ለውጤታማነቱ ምንም ዓይነት አስተማማኝ የሆነ ተጨባጭ መረጃ ባለመኖሩ ፖሊሲ አውጪዎች በዓለም ዙሪያ ሁሉን አቀፍ የጾታ ትምህርትን ለመተግበር ያወጧቸውን እቅዶች እርግፍ አድርገው በመተው በጉርምስና ዕድሜ ላይ በሚገኙ ልጆች ላይ የወሲባዊ ልምምዶች የሚያስከትሏቸውን መጥፎ ውጤቶችን ለመቀነስ ሌሎች አማራጭ ዘዴዎችን እንዲጠቀሙ እንመክራለን። የመታቀብን አዎንታዊ ውጤቶችን በተመለከተም ተጨማሪ ጥናቶች መደረግ አለባቸው።"

**ለማጠቃለል ያህል ውጤት አልባ መሆኑ በማያሻማ ሁኔታ የተረጋገጠውንና እና ከፍተኛ ውዝግብ ያስከተለውን ሁሉን አቀፍ የወሲብ ትምህርትን (CSE) በት/ቤቶቻችን ውስጥ ለማቅረብ ምንም ዓይነት ህጋዊ ግዴታ የለብንም ፤ ከህብረተሰብ ጤና አጠባበቅ አንጻርም ሁሉን አቀፍ የጾታ ትምህርት (CSE) ጠቃሚ ውጤት ስለማምጣቱ የተጨበጠ ማስረጃም የለም። ከነዚህ ሁሉ አስደንጋጭ እውነታዎች አንፃር እኛ ፊርማችንን ከዚህ በታች ያሰፈርን ዜጎች የኢትዮጵያ መንግስት እና በተለይም የትምህርት እና የጤና ሚኒስትሮቻችን የሚከተሉትን ሰባት እርምጃዎች በአስቸኳይ እንዲወስዱ በአክብሮት እንጠይቃለን ።**

1. ኢትዮጵያ ሐገራችን ከሌሎች የምስራቅና ደቡባዊ አፍሪካ ሐገራት ጋራ የሁሉን አቀፍ የጾታ ትምህርትን (CSE) ተግባራዊ ለማድረግ ከፈረመችው ስምምነት (Eastern Southern Africa Commitment on CSE) በፍጥነት እንድትወጣ (የCSEን አጀንዳ ሳይረዱ የፈረሙ በርካታ የአፍሪካ አገራት አሁን ለመልቀቅ እየሰሩ ናቸው።)
2. አወዛጋቢ የሆነውን የብሔራዊ የጎልማሶች ወሲባዊ እና የተዋልዶ ጤና እና መብቶች ማዕቀፍ ስትራቴጂን (National Adolescent Sexual and Reproductive Health and Rights (ASRHR) Framework Strategy) ተግባራዊ ከማድረግ እንድንቆጠብ
3. በሙሉም ሆነ በከፊል የሁሉን አቀፍ የወሲብ ትምህርትን (CSE) ሐሳብ የያዙ የተጀመሩም ሆነ በዕቅድ ላይ ያሉ ፕሮግራሞች ሁሉ እንዲወገዱ ( ሁሉን አቀፍ የወሲብ ትምህርት (CSE) የሚያካትታቸውን 15 ጎጂ ሐሳቦች በhttps://www.comprehensivesexualityepted.org/wp-content/uploads/Harmful-Effects-10.17.17.pdf ላይ በመሄድ ይመልከቱ)

4. ወላጆች እና አሳዳጊዎች የልጆቻቸውን የጾታ ትምህርት በመምራት ፣ በመቅረጽ እና በመቆጣጠር ረገድ ያሏቸው መብቶች እውቅና እንዲሰጣቸውና እንዲከበሩ
5. በኢትዮጵያ ውስጥ ከእንግዲህ ማንኛውንም ዓይነት የሁሉን አቀፍ የወሲብ ትምህርት (CSE) ይዘቱ እየተቀየረ በተለያየ መልክ ወደ ሥርዓተ ትምህርታችን በማንኛውም መልክ እንዳይካተት
6. ከማንኛውም ዓይነት የወሲብ ባህሪ መታቀብን (በወሲብ ድርጊት ተሳታፊ የሆኑትን ወጣቶችን ደግሞ ወደመታቀብ እንዲመለሱ ማድረግን) በሁሉም የወሲብ ሥርዓተ-ትምህርት እና መርሃግብሮች ውስጥ በዋናነት አቋም ተደርጎ እንዲደገፍ
7. የትኛውም የኢትዮጵያ የሕዝብም ሆነ የግል ትምህርት ቤት በየትኛውም የትምህርት መመሪያው ውስጥ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ጉዳዮችን ማካተት እንደማይችል ማረጋገጥ፡-

ሀ. በልጆች መካከል የሚደረግ ወሲባዊ ተግባርን ኖርማል እንደሆነ ማስተማር ወይም ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች በወሲባዊ ተግባር ውስጥ ሲሳተፉ የሚያሳይ ወይም የሚገልጽ ምሳሌዎችን መጠቀም

ለ. ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች መካከል የሚደረግ ማንኛውም ዓይነት ወሲባዊ ተግባር ከጠንቅ የፀዳ ወይም አደጋ የሌለው ሊሆን እንደሚችል መጠቆም

ሐ. ስለ ግለወሲብ (Masturbation) ወይም በአፍ ወይም በፊንጢጣ ስለሚደረጉ ወሲባዊ ግንኙነቶች የሚገልጹ ቁሳቁሶችን ወይም ይዘቶችን በትምህርት ውስጥ ማካተት

መ. ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን ከጥቃት ለመከላከል የሚያስችላቸውን መንገዶች ከማሳየት ባለፈ ወሲባዊ መብቶች እንዳሏቸው የሚያመለክቱ ሐሳቦችን ማንጸባረቅ

ሠ. የሚከተሉትን አሉታዊ የሆኑ የጾታዊ ማንነት (gender Identity) ፅንሰ-ሀሳቦች፣ ቁሳቁሶችን ወይም ይዘቶችን ማካተት

i. ጾታ ሊለወጥ የሚችል ነው፤
ii. ጾታ ቋሚ አይደለም፤
iii. ጾታ በተፈጥሮ ሳይሆን በራስ የሚወሰን ነው፤
iv. ከወንድ እና ከሴት ውጪ ሌሎች ጾታዎች አሉ፤
v. የወንዶች እና የሴቶችን ተውላጠ ስሞች በመቀያየር እንዲጠቀሙ ማበረታታት
**vi.** ልጆች በወሲባዊ ምርጫቸው (sexual preference) መሠረት እንዲለዩ ማበረታታትን **የመሣሠሉ አመለካከቶችን ማራመድ ፈጽሞ ተቀባይነት እንደሌላቸው እንዲታወቅ እንሻለን።**

ከጾታ ማንነታቸው ጋር ለሚታገሉ ልጆች ርህራሄ እና ድጋፍ ሁል ጊዜም መሰጠት እንዳለበት በጽኑ እናምናለን ፣ ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱ ርህራሄ ሕፃናትን ከእውነታው ተቃራኒ ወደሆነ ማንነት እና ለህይወት ዘመን መካንነት ወደሚዳርጋቸው የህክምና ጣልቃ ገብነት እና ቀዶህክምና በማምራት በሐሰት እምነት አስሮ ሊቆልፍባቸው አይገባም። **ስለሆነም ቀደም ሲል የተጠቀሱትን እርምጃዎች በመውሰድ የኢትዮጵያን ልጆች ለመጠበቅ አስቸኳይ እርምጃ እንዲወሰድ በአክብሮት እንጠይቃለን ።**

**የሀገራችን የወደፊት ዕጣና የልጆቻችን የወደፊት ሕይወት አደጋ ላይ ነው!**

**ከሠላምታ ጋር ፣**

**ፊርማዎትን**

**https://www.comprehensivesexualityeducation.org/international-map/ethiopia/ ላይ በመሄድ ያስፍሩ**

**የኢሜይል አደራሻ (ፊርማዎን ይወክላል)**

**ስም**

**የአባት ስም**

**የስልክ ቁጥር**

**ፊርማዎን ያስገቡ(Submit)**